# የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ

PRINTED BY
International & Public Relations Directorate

OCT 2020

Monthly Newsletter Vol 17 No.2

# 13ኛው የሰንደቅ ዓላማ ቀን በኢ.ሲ.ሰ.ዩ. ተከበረ



"ሰንደቅ ዓላማችንለ ሰላማችን ለአብሮነታችንና ለሃገራዊ ብልጽግናችን!"



TCD Gives Training

የተማሪዎች ቅበላ ቅድመ ዝግጅት በኢ.ሲ.ሰ.ዩ.

ECSU Community Radio Station Gives Training



## ራዕያችን

የሀገራችንን ልማትና ትራንስፎርሜሽን እውን ለማድረግ ቀልጣፋ፣ ውጤታማ፣ ግልጽና ተጠያቂነት ያለው ፐብሊክ ሰርቪስ ከመገንባት አኳያ በ 2017 በአፍሪካ የልህቀት ማዕከል መሆን

## ተልዕኳችን

ፐብሊክ ሰርቪሱ የአገልጋይነት መንፈስ የተላበሰ እና በግልጽነትና በተጠያቂነት የሚሰራ እንዲሆን አቅሙን በስፔሻላይዝድ ትምህርት፣በስልጠና፣ በማማከር፣በምርምር እና ማህበረሰብ አገልግሎቶች በቀጣይነት መገንባት

## እሴቶቻችን

ተገልጋይ ተኮር
ቁርጠኝነት
ሁሌም መማር
ብዝሀነት መቀበል
ትኩረት ልዩ ድጋፍ ለሚሹ
አሳታፊነት
ተባብሮ መስራት

## Our Vision

To become a leading center of excellence in public service capacity building in Africa by 2025 through building efficient, effective, Transparent and accountable public service which can contribute to the realization of the development and transformation drive of the country

## Our Mission

Enhancing the service orientation, transparency and accountability of the public service by building its capacity through Specialized Education,Training, Consultancy, Research and Community Services.

## Our Values

Customer Focus
Commitment
Continuous Learning
Welcoming Diversity
Attention to the Disadvantaged
Participation
Collaboration

# Ethiopian Civil Service University

## Content


1. ECSU Celebrates the 13thNational Flag Day
2. Training Coordination Directorate Gives Training
3. ECSU Community Radio Station Gives Training
4. ICT Directorate Gives IFMIS Training
5. የተማሪዎች ቅበላ ቅድመ ዝግጅት በኢ.ሲ.ሰ.ዩ.



**Photos**
Ibsa Bekele
Dereje Tesfaye

**Editor In -Chife**
Tariku Ayano

**Editors**
Anteneh Demisse
Meley Tekeste

**ግራፊክስ እና LAYOUT DESIGN**
Dereje Tesfaye


## የዝግጅት ክፍሉ መልእክት

የኮቪድ 19 ቫይረስ ወደ ሀገራችን መግባቱ ከተረጋገጠበት ጊዜ አንስቶ እንደ ሀገርም ሆነ በዩኒቨርሲቲያችን ደረጃ ማህበረሰቡን ከወረርሺኙ ለመታደግ በርካታ የጥንቃቄ ስራዎች ሲከናወን መቆየቱ የሚታወቅ ነው፡፡ ሆኖም የወረርሽኙ ስጋት እንደታሰበው በአጭር ጊዜ የሚወገድ አለመሆኑን ከግምት ውስጥ በማስገባት ቀደም ሲል ተቋርጦ የነበረው መደበኛ ስራና እንቅስቃሴ ወደነበረበት ሁኔታ በበመለስ ላይ ይገኛል፡፡ ይህ ደግሞ በማህበረሰቡ ዘንድ መዘናጋትን እያስከተለ መሆኑ በገሀድ እየታየ ነው፡፡ በመሆኑም መላው የዩኒቨርሲቲያችን ሰራተኞች የኮረና ቫይረስን አደገኛነት በመገንዘብ፤ እራሳቸውንና ማህበረሰቡን ከወረርሽኙ ለመከላከል በሚያደርጉት ጥንቃቄ ላይ ምንም አይነት መዘናጋት እንዳይኖር፤ የመማር ማስተማር ስራውም በመደነኛነት በሚጀመርበት ወቅት ለተማሪዎቻችንም አርአያ በመሆን የመከላከል እንቅስቃሴውን በተግባር እንዲደግፉ የጠበቀ መልዕክታችንን ለማስተላለፍ እንወዳለን፡፡

ውድ አንባቢያን ለቀጣዩ ወር ዕትም ጽሁፍ ማበርከት የምትፈልጉ ሁሉ ህንጻ ቁጥር5 ቢሮ ቁጥር 210 ድረስ በአካል በመምጣት ወይም በኢሜል pr.ecsu@gmail.com አድራሻችን በመላክ መሳተፍ የምትችሉ መሆኑን በአክብሮት እናሳውቃለን፡፡በተጨማሪ የኤሌክትሮኒክስ ወርሃዊ ህትመታችንን በ ድህረገጻችን (www.ecsu.edu.et) GALLERY (Megazine and Newsletter) በሚለዉ ስር ታገኛላቹ ፡፡

**ዝግጅት ክፍሉ**

# ECSU Celebrates the 13th National Flag Day

Ethiopian Civil Service University community celebrated the 13th National Flag Day on Monday October 2, 2020 at the main campus of the university. The day was also celebrated at the national level under the theme of "Our flag for our peace, unity and national prosperity".





On the program, it is indicated that our flag symbolizes our common history and unity. Respecting, nurturing and protecting our national flag disclose our respect and loyalty to the people and the country that we love. So the celebration of this day helps us to further strengthen our peace and development, and we as citizens must stand together and strive for overall national prosperity.





It is known that national Flag Day has been celebrated for the last thirteen years annually by federal and state institutions in accordance with the directives and guidelines issued by the House of Peoples' Representatives to ensure our continued peace, unity and prosperity.

At the ceremony members of the Federal Police Commission presented a demonstration and due to the COVID 19 threats, limited numbers of ECSU community participated.

# Training Coordination Directorate Gives Training

Training Coordination Directorate organized two days training on "online and digital materials support" for trainers and consultants from October 01-02, 2020 at Hidasse Hall. The training was given by Dr. Birhahu Beyene and about twenty five trainers and consultants under training and consultancy division participated.



**Dr. Birhanu Beyene**
*Trainer*



According to Dr. Birhanu, the training was the second part of the three phases training focused on: Basics of E-training, E-training Instruction Design and Online Training Facilitation. The training was designed to assist the directors and training experts to facilitate the digital content development, redesigning and preparation of e-learning materials. On the training, it is explained why blended learning is important in this fourth generation. In addition, technical issues related to information technology like content development, learning methodology design, evaluation and assessment as well as networks and participants in the process have been indicated as the basic principles of the e-learning.

He also indicated that the training is a project based training and in the first phase the review of the existing training materials and the extent to which the materials need to be redesigned have been identified. Based on the identified results, the existing training materials will be redesigned to make them suitable for online training and direct to pave the way for the preparation of the strategic plan and online training policy.





# ECSU Community Radio Station Gives Training


Ethiopian Civil Service University Community Radio Station gave induction training to its new staff from Sep 28 to Oct 1, 2020 at the station.





**W/ro Mihret Kassa**
*Manager of the Community Radio Station*

The training was designed to introduced the new staff about editorial policy, procures and guidelines of the station. Besides, it gave detail information about the purpose and goal of the radio station, how to provide up-to-date information to the community, what a vital role Community radio plays in the community and how to serve the community through community radio station .The training was given by senior ECSU community Radio 100.5 station journalists.








W/ro Mihret Kassa, Manager of the Community Radio Station, said that the training will continue in the future to update the journalists in service training form.

# ICT Directorate Organizes IFMIS Training





Ethiopian Civil Service University ICT Directorate gave IFMIS training using zoom online technology on "Usage of IFMIS system for Self-service users" from 29 to 30 August 2020 at ICT Computer Lab. The purpose of the training was to train employees on how to use practically IFMIS self-service users system which embrace move order, Purchase requisition and other services.




Ato Yitbarek Ibrahim, Information Communication Technology Directorate Director, said the training is believed to enable the trainees to use IFMIS self-service user functions effectively. He also noted that on IFMIS's other functions persistent training will be organized in collaboration with MoFED to build the capacity of the staff in using IFMIS all functions.



On the training more than 60 administrative staff from each College and Directorate participated and it is the fourth round training, each round lasts for two days.

# SGS Organizes PhD Defense Program

Ethiopian Civil Service University School of Graduate Studies organized PhD defense program on October 05, 2020 at Hidasse Hall.

On the program, the candidate Ato Dawit Gebremedihin, presented his PhD dissertation paper entitled "A Study on Tax Audit and Tax Compliance in Ethiopia; the case of Addis Ababa City Government Revenue Authority" at the presence of internal and external examiners and he defended for the questions forwarded by the examiners.



**Ato Dawit Gebremedihin**
*Doctoral Candidate*





As the result of the defense, the Examination Board for Doctoral Dissertation Defense announced that the candidate has been awarded PhD degree.







# የተማሪዎች ቅበላ ቅድመ ዝግጅት በኢ.ሲ.ሲ.ዩ.

የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የኮረና ቫይረስ ወደ ሀገራችን ከገባበት ጊዜ አንስቶ የዩኒቨርሲቲውን ማህበረሰብ ከወረርሺኙ ለመታደግ ከመንግስት የሚሰጠውን አቅጣጫን መሰረት በማድረግ የተለያዩ ተግባራትን ሲያከናውን ቆይቷል፡፡ በተለይም የመማር ማስተማር ስራውን በአካል ከሚደረግ ንክኪ ነጻ ለማድረግ በተወሰነው ውሳኔ መሰረት ተማሪዎች ክፍል ገብተው ከመምህራንና እርስ በርሳቸው የሚያደርጉትን የፊት-ለፊት ግንኙነት እንዲያቆሙና በየዶርማቸው ሆነው ከመምህራኖቻቸው በኢሜይል፣ በቴሌግራም እና በመሰሰሉት ዘመናዊ የኤልክትሮኒክ የመገናኛ መሰሪያዎች አማካይነት የሚላኩላቸውን የትምህርት ማቴሪያሎችን እንዲከታተሉ ማድረግ የመጀመሪያው እርምጃ ነበር፡፡ ከዚያም በማስከተል ተማሪዎች ወደየክልላቸውና ወደየቤተሰቦቻቸው እንዲመለሱ ተደርጎ የመማር ማስተማር ስራው በኦን ላይን የቀጠለ ሲሆን ተማሪዎች በየክልላቸው ሆነው ከመምህራን ጋር ግንኙነታቸውን በማጠናከር በተለይ የምርምር ስራዎቻቸውን እንዲያጠናቅቁ ለማድረግ ከፍተኛ ስራ ተሰርቷል፡፡

ከዚሁ ጎን ለጎን በዩኒቨርሲቲው በተቋቋመው የኮቪድ 19 መከላከልና መቆጣጠር ግብረ ኃይል አማካኝነት ሰራተኛውን ከበሽታው ለመከላከል የሚያስችሉ ልዩ ልዩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችም ተሰርተዋል፡፡ በሰራተኞች ካፊቴርያ ቋሚ መረጃ የሚሰጡ ፕሮግራሞችን በሞንታርቦ አማካኝነት የማስተላለፍ፤ ልዩ ልዩ ፖስተሮችን በግልጽ በሚታዩ ቦታዎች ላይ መስቀል፤ ልዩ ልዩ ብሮሹሮችን በማዘጋጀት ለዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ማሰራጨት እንዲሁም በየወሩ በሚታተሙ ዜና መጽሄቶች ላይ ግንዛቤ የሚፈጥሩ ጽሁፎችን የማዘጋጀት የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች የተሰሩ ሲሆን በሽታውን ለመከላከል የሚያስችሉ የንጽህና መጠበቂያ ቁሳቁሶችን በማቅረብ ማህበረሰቡን ከወረርሽኙ ለመከላከል ከፍተኛ ጥረት ተደርጓል፡፡

ሆኖም የወረርሽኙ ስጋት እንደታሰበው በአጭር ጊዜ የሚወገድ አለመሆኑን ከግምት ውስጥ በማስገባት የመማር ማስተማር ስራው በመደበኛነት እንዲቀጥል በመንግስት በተሰጠው አቅጣጫ መሰረት ዩኒቨርሲቲው በ2013ዓ.ም መደበኛውን የመማር ማስተማር ስራው ለመጀመር ቅድመ ዝግጅቱን በተገቢው ሁኔታ በማጠናቀቅ ላይ ይገኛል፡፡ ለዚህም በሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር አማካይነት በተዘጋጀው የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የኮቪድ 19ን የመከላለክ ተግባርን ማዕከል ባደረገ መልኩ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ከመከፈታቸው በፊት እንዲሟሉ ተቀርጾ በቀረበው ፕሮቶኮል መሰረት በርካታ ስራዎች በመሰራት ላይ ናቸው፡፡ ለአብነት ያህልም በተቋሙ በ2013 ኮቪድ 19 ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችል ልዩ እቅድ አዘጋጅቶ እና በፈጻሚ አካላት ዘንድ ተገቢውን ግንዛቤ ፈጥሮ ወደ ስራ ገብቷል፡፡

በተማሪዎች ዶርሚተሪ፣ የመመገቢያ አዳራሽ፣ ካፊቴሪያዎች፣ ክሊኒክ፣ የተማሪዎች የመማሪያ ክፍሎች፣ ቤተመጻህፍት እና ሌሎችም አገልግሎት መስጫ ስፍራዎች ላይ አስፍላጊው የቅድመ ጥንቃቄ እና የቅድመ ዝግጅት ስራዎች በኮቪድ 19 መከላከልና መቆጣጠር ግብረ ኃይል አማካይነት እየተሰራ ይገኛል፡፡ ግብረ ኃይሉ ቀደም ሲል የሰራቸው ስራዎች እንዳሉ ሆነው ሌሎችም በፕሮቶኮሉ ውስጥ የተቀመጡ ዝርዝር ተግባራትንም በሙሉ ለማሳካት ስራዎች በመሰራት ላይ ናቸው፡፡ መምህራንና ሁሉም የድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች 2013 የለትምህርት ዘመን ሪፖርት አድርገው በሥራ ላይ የሚገኙ ሲሆን ግብረ ኃይሉ ኮቪድ 19ን ከመከላከልና ምላሽ ከመስጠት አንጻር ከጤና ሚኒስቴር፣ ከሠላም ሚኒስቴር፣ ከህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩትና ከአደጋ ስጋትና ሥራ አመራር ኮሚሽን ጋር በጋራ እየሰራ ይገኛል፡፡

በሌላ በኩልም አስፈላጊ የሆኑ ግብዐቶችንና መሰረተ ልማትን ከማሟላት ጋር በተያያዘም ከሚመለከታቸው የውሃና መብራት ኃይል ጋር የግንኙነት ሥርዓት ተፈጥሯል፡፡ ቀደም ሲል ከነበረው የደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ

ማስወገጃ ሥርዓትና መሠረተ ልማት ተጨማሪም ሌሎች የደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃዎች የሚዘጋጁ ይሆናል፡ ፡ የዩኒቨርስቲው የህክምና አገልግሎት መስጫ መካከለኛ ክሊኒክ አገልግሎት እየሰጠ ሲሆን ከክሊኒኩ አቅም በላይ የሚሆኑ ህክምናዎች በሚያስፈልጉ ሰዓት ከሚኒልክና ከጥቁር አንበሳ የሪፈራል የህክምና አገልግሎት በየዓመቱ የሚታደስ ውል በመኖሩ የከፋ የጤና ችግር የሚገጥማቸው ተማሪዎች በዚያ የሚስተናገዱ ይሆናል፡፡

በዩኒቨርሲቲው የውሃ አቅርቦት ቢኖርም የውሃ አቅርቦት ሽፍት በሚሆንበት ጊዜ በሮቶ በመጠቀም እንዲሁም በቦቴ ለመግዛት ከውሃና ፍሳሽ ጋር የውል ስምምነት የተገባ ሲሆን በተጨማሪም ዩኒቨርስቲው የራሱን የውሃ ጉድጓድ አስቆፍሮ የመስመር ዝርጋታ ለማድረግ በሂደት ላይ ይገኛል፡፡

በቀጣይም ከንክኪ ነጻ የሆኑ የእጅ መታጠቢያዎች የመግቢያ በር፣ መመገቢያ አዳራሽ፣ በላውንጅ፣ በመኝታ ህንጻዎች እና በመማሪያ ክፍሎች ለማዘጋጀት ቅድመ ዝግጅት ሥራዎች እየተሰሩ ናቸው፡፡ ተማሪዎች ከመግባታቸዉ በፊት የሳሙናና ጸረ ተህዋሲያን አቅርቦት የተዘጋጀ ሲሆን ለቀጣይ የሚያስፈልጉ ግብአቶች በተዘጋጀው እቅድ ላይ ተመላክተዋል፡፡ የኢንፍራ ሬድ ሙቀት መለኪያ ለመግዛት ቅድመ ሥራዎች እየተሰራ ነው፡፡

ኮቪድ 19ን በተመለከተ ለዩኒቨርስቲው ማህበረሰብ በቂ ግንዛቤ የሚፈጥርና መረጃ የሚሰጡ የኮሚኒኬሽን ዝግጅቶች በዩኒቨርስቲው ዌብሳይት፣ facebook በተጨማሪም በተቋሙ ማህበረሰብ ሬድዮ እየተሰሩ ይገኛል፡፡ የተቋሙ ድህረ-ገጽ የተሻሻለና ስለኮቪድ 19 መረጃ የሚሰጥ ሲሆን ለኮቪድ 19 በቂ የማስታወቂያ ሊፍሌቶች ፣ ፖስተሮች ፣ ብሮሸሮች የተዘጋጁ ሲሆን ባነሮች በመዘጋጀት ላይ ናቸው፡፡

በተቋሙ ማህበረሰብ ላይ የተለያዩ የበሽታ ምልክቶች ቢያስተውሉ ደውለው የሚያሳውቁበት መንገድ ከ8335 በተጨማሪ / የተማሪዎች አገልግሎት ዳይሬክቶሬት፣ አለምአቀፍና ህዝብ ግንኙነት ዳይሬክቶሬት ስልኮች አገልግሎት የሚሰጡ ይሆናል፡፡ ለጽዳት አገልግሎት ሠራተኞች በወረርሽኙና መከላከያ መንገዶቹ ዙሪያ በቂ ግንዛቤ ተፈጥሯል፡፡

የመማር ማስተማሩን እንቅስቃሴ ከወረርሽኙ ስጋት ነጻ ለማድረግ ለአገልግሎት መስጫ ክፍሎች /መማሪያ፣ ማንበቢያ ስፍራዎች/ የጽዳት ግብዓቶች ወረርሽኙን ታሳቢ ባደረገ መልኩ እየተዘጋጁ ይገኛል፡፡ የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ቅርጫቶች በበቂ ሁኔታና ርቀት ላይ ተዘጋጅተዋል፡፡ በመማሪያ ክፍል የተማሪዎች አቀማመጥ ከመጻፊያ ሰሌዳ እና ከፊት ረድፍ መካከል ቢያንስ አንድ ሜትር ተኩል ርቀት የሚኖረው ሆኖ ተዘጋጅቷል፡፡ ካፌቴሪያ ላይ ርቀት መጠበቂያ ምልክት ያለባቸው መጠቆሚያዎች ተዘጋጅቷል፡፡ አገልግሎት መስጫ ክፍሎችና ስፍራዎች ተማሪዎች ወደተቋሙ ግቢ ከመግባታቸው በፊት በተገቢው ማጽጃ ዘዴዎች ለማጽዳት ዝግጅት የተደረገ ሲሆን በመግቢያ በር፣ አገልግሎት መስጫ ስፍራዎችና ሌሎች ፍተሻ በሚከናወንባቸው ቦታዎች ለፈታሾች የእጅ ጓንት፣ የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ ጭምብል ተዘጋጅቷል፡፡ በዩኒቨርስቲው የሚከናወኑ ተግባራትን ከንክኪ ነጻ ለማድረግና የቫይረሱን ስርጭት ለመከላከል የሚያስችሉ በርካታ ስራዎች በስፋት እየተሰሩ ሲሆን ለዚህ ተግባር የሚያገለግሉ የተለያዩ ቁሳቁሶችንም ለማሟላት በግዢ ሂደት ላይ ነው፡፡

በአጠቃላይ ዩኒቨርሲቲው በሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር በተላከው ፕሮቶኮልና በተቀመጠው ቼክ ሊስት መሰረት ተማሪዎችን ለመቀበልና የፊት ለፊት የማስተማር ስራውን ለመጀመር የሚጠበቅበትን ቅድመ ዝግጅት በሚገባ እያከናወነ ይገኛል ፡፡ የተሰሩት ስራዎችም የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በቅርቡ በተቋሙ ቅድመ ዝግጅት ላይ በሚያደርገው ጉብኝትና ከጉብኝቱ በሚገኝ ግብረ መልስ መሰረትም በጥቅምት ወር ዩኒቨርቲው ተማሪዎችን ተቀብሎ የመማር ማስተማር ስራውን የሚጀምር ይሆናል፡፡

ስለዚህ የዩኒቨርስቲው ማህበረሰብ ልብ ሊለዉ የሚገባዉ ዋናዉ ነገር ወረርሽኙን እየተከላከሉ ተማሪዎችና ሰልጣኞች ሳይዘናጉ የሰራተኛዉ ደህንነት እየተጠበቀ የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር ና የጤና ሚኒስትር ባስቀመጡት ሂደት ትምህርት ማስቀጠል የተቋሙ ማህበረሰብ ሀላፊነት ጭምር ነዉ፡፡ ጤናችን በእጃችን!!

# ዜና እረፍት



## አቶ አስራት አማረ

የዩኒቨርስቲያችን ባልደረባ የሆኑት አቶ አስራት አማረ ባጋጠማቸዉ ድንገተኛ ህመም ምክንያት ከዚህ አለም በሞት የተለዩ ሲሆን መላዉ የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ማኅበረሰብ በአቶ አስራት አማረ ህልፈት የተሰማንን ጥልቅ ሀዘን እየገለፅን ለቤተሰቦቹና ወዳጅ ጓደኞቹ መፅናናትን እንመኛለን፡፡

## የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ

## International and Public Relations Coordination Directorate

**Contact Address:**

Tel.0116 46 2887,Extension: 253/252/257 , Fax: 0116463016

P.O.Box5648, E-mail: www.Iprd @ecsu.edu.et ,

Website: www.ecsu.edu.et, Tweeter: @ECSU tweets ,FM Radio:-100.5MHz

Facebook: Ethiopian Civil Service University




BUILDING CAPACITIES IN PUBLIC SECTOR SINCE 1995

**PRINTED BY** *International & Public Relations Directorate*